# <u>አድዋ</u>

የአፍሪካ ጀግና መጠሪያ
        የፍልሚያ አምባ ረሞጪ:
የቅኝ አገዛዝ ማፈሪያ
        የጎበዝ ህዝብ እልህ መውጪ።
ዙሪያ ገባሽ ወንዛወንዙ
        ጋራ ተራራሽ ሸንተረሩ:
ቁልቁል ሽቅብሽ አድማስ ጪፉ
        አይን አይታክቴ ዱሩ።
የሰናድር የወጨፎው
        ያልቤን የረሹ    የመውዜሩ:
የዲሞትፈር የቼኮዙ
        የእከደከው አረሩ።
የተወናጨፈብሽ አምባ
        አንቺ የጎጥ ቀዬዋ:
የጥቁር ህዝብ አሻራ
        የሃበሻ ምድር አድዋ።
ስንቱ ደሙ ቀለመብሽ
        ስንቱ ለስምሽ ተሠዋ:
የጥቁር ህዝብ መስተዋቱ
        ኢትዮጵያዊቷ አድዋ።
ከቦረና አባ ዋሪዎ
        ከጉጂ ሲዳማ ጎዳና:
ከከምባታ አባ ሓደሮ
        ከወላይታ አባ ጦና።
ከከፋ እነአባቢያ
        ከወለጋ አባ ሞሲሳ:
ከጋሞ እነጋሎሬ
        ከአምቦ እነአባ ጪብሳ።
ከጉራጌ እነደንድር
        እነአዝብጤ ሰሜን ሸዋ:
ከሃረርጌ እነሙስጠፉ
        ከጋምቤላ እነጀሹዋ።
ከባሌ እነአባከድር
        ከወሎ እነይመሬ:
ከጎጃም እነማስተዋል
        እነአስማማው ጎንደሬ።
ካፋር ከኢሳ እነአብዲ
        ከአሩሲ እነቡሽራ:
እነተወልደ ከትግራይ
        እነዘኪሮስ ከኤርትራ።
የወደቁልሽ አምባ
        ያድዋ ዱርና ጋራ:
እስቲ መስክሪ ሃቅሽን
        ነሽና የታሪክ አሻራ።
አፈርሽ ያበሻ ደምን
        መቼም መጠት አልደረቀ:
እድሜሽ ምዕት ቢሞላው
        ወዝሽ ገርጥቶ አላለቀ።

አድዋ....
እንዴት ነበረ ንገሪን
ከሶላቶ ጋር ትንንቁ፡
ጀግኖችሽ ግዳይ ሲጥሉ
በጣሉት ጠላት ላይ ሲወድቁ።
እንዴት ነበረ ወኔያቸው፡
አምባሽን ላለማስደፈር
ቃል ሲገቡ በየምኒታቸው።
ጦር ሰብቀው ሲወረውሩ
እንዴት ነበረ ሲማማሉ፡
ወንድና ሴቱ ተደጋግፈው
የጣሊያን ግዳይ ሲጥሉ።
ጣይቱና ምኒልክስ
ከቶ ምንድነው ያሉ፡
ሞላው ኢትየጵያ ሲንቀሳቀስ
በሲቃ ሲተም ጀግናው ሁሉ፡
ጣይቱና እምዬ ከቶ ምንድነው ያሉ።
አድዋ ......

የሶላቶ መድፍ ሲያርስሽ
እምቢታሽ እንዴት ነበረ፡
በየስርጣሰርጡ ስር
ስንት ጀግና ነው የቀረ?።
አይማረኝ ከማርኩት ብሎ
ስንቱ ጀግናሽ ተጋፈጠ፡
በቅኝ አገዛዝ ጥላቻ
ስንቱ እምቢ ባይ አጠጠ፡
ለሞት ዳረጎት ፈገግ ብሎ
ከፋመው እሳት ተረመጠ።
የሂሳ ደጀን ወይዛዝርትሽ
በርታ እያሉ ከሁዋላ፡
ወኔ ሲሞሉት ሰራዊቱን
ስንቱ ጥይት ስንቱን ቆላ።
ይብላኝ ላድር ባዩ እንጂ
ለሹምባሹ ለከርሳሙ፡
የትብቱን ቀዬ ለሸጠ
ክዳት ለሆነ ስሙ።
አድዋ....
እንዴ ነበረች ቅፅበቷ
የጀግናው ሲቃ ቁጣ፡
ሳንጃ ባፈሙዝ ወድሮ
ሲቀላቀል በጨበጣ፡
ሲሞሻለቅ ሲተራረስ
ከመድፉ አፍ ላይ ሲወጣ።
እንዴት ነበረ ኢትየጵያዊ
ምንድን ነበረ እምነቱ፡
ለምን ነበረ ማለቁ
ለምን ነበረ ሞቱ።

እስቲ ውነቱን ንገሪን
ለማተብሽ ብለሽ አድዋ:
ለምን ኢትዮጵያዊው ሞተ
ለምን ህይወቱን ሰዋ::
ከደቡብ ሰሜን ተንቀሳቅሶ
ከምስራቅ ምዕራብ ተንቀሳቅሶ:
አመሉን በጉያው ከቶ
ስንቁን ባህያ አንግቦ:
ለምን መንደሩን ትቶ
ስንቱን ፈፋ አቍርጦ:
ስንቱን ወንዛወንዝ ተሻግሮ
ወገቡን በሸክም አጉብጦ::
እልፍ አዕላፍ ኢትዮጵያዊ
ለምን ለጥሪሽ ተሰለፈ:
ደረቱን ለእርሳስ አረር
አንገቱን ለድል ሰየፈ::

ለምን አድዋ ለምን
ጀግናሽ ጠላቱን ፈጀ:
ባፈሰሰው ደሙ ብስራት
ለምን ኢትዮጵያን ዋጀ:
ለምን አፍሪቃን ዋጀ::
ምንድን ነበረ ሚስጢሩ
ጥቁሩ የሃበሻ ዘር:
ከነጩ ጋራ ፍልሚያው
የተቆላው በአረር::
ምነዋ ... አፍሪቃ ደስ አላት:
ሲሰማ ያድዋ ብስራት:
አድዋ...
የጥቁር ህዝብ እልልታ
የነጭ ወራሪ ስብራት::
ሶላቶ.....
በእብሪት እንደጎመጀ
በግፍ እንደወረረ:
ሳይሰበሰብ ምራቁ
ተዝረክርኮ ለምነ ቀረ::
ምንድን ነበረ ኢትዮጵያዊ
የእምነት የወኔ ትጥቁ:
ስንትስ ነበረ ጠብመንጃው
ስንትስ ነበረ ጥይቱ:
እንከምን ነበር ግቡ
ከቶ ምን ነበር እምነቱ::
አሻፈረኝ ያሰኘው ኪዳን
ያልተረዳነውን ገበና:
እስቲ ንገሪን አድዋ
የታሪክ አሻራ ነሽና::

... አድዋ
መልእክትሽ ምንድነው ዛሬ
        ትዝታሽ ትዝብት ሆኖ፡
ልጆችሽ ሲናቆሩብሽ
        አንድነታቸው ተበትኖ።
አይንሽ ምንድን ያስተውላል
        ከቶ ምን ይላል አንደበትሽ፡
አያሳይ የለው ዘመን
        እንቲ ተጠየቂ እንጠይቅሽ።
አረንጓዴና ቢጫ ቀዩን
        ሰንደቅሽን ከፊት ይዞ፡
ጎራዴውን ከሰናድር
        ሰይፉን ካፎቱ መዞ።
እንዲያ ሲወድቅ ሲነሳ
        ትዝም አይልሽ ከቶ፡
ስምሽን ተክሎልሽ ሲያልፍ
        ህይወቱን ላንቺ ሰውቶ።
አድዋ...
ይብላኝልሽ እንጂ አድዋ
        ለያዘሽ ገትጋታ አባዜ፡
ሰኔና ሰኞ ሲሆንብሽ
        ክፉ ዳኛና ጊዜ።
ይብላኝልሽ አደዋ
        ያልታደልሺው የወላድ መካን፡
ሰቆቃ ሲዳምንብሽ
        መጦሪያሽ የርግማን ሲሆን።
ይብላኝልሽ አድዋ
        ይብላኝልሽ !!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!

**ምንተስኖት መንገሻ**
**Mentesnot Mengesha (2006)**

የደራሲው መብት በህግ የተከበረ ነው።